Seattle Neighborhoods

# የዜና ሥርጭት

**የሚዲያ ግንኙነት:** ሳም ሪድ (Sam Read)፣ 206.727.8808፣ sam.read@seattle.gov

## የሲያትል የወረዳዎች መልሶ ማከፋፈል ኮሚሽን በአዲሱ የከተማ ምክር ቤት ወረዳዎች ረቂቅ ካርታ ላይ የህዝብ አስተያየት ይፈልጋል

**ሲያትል** (ነሐሴ 3 ቀን 2022) – የሲያትል የወረዳዎች መልሶ ማከፋፈያ ኮሚሽን በአሁኑ ጊዜ የሲያትል ሰባት የከተማ ምክር ቤት ወረዳዎችን ድንበሮች እንደገና ስሎ ለማስተካከል በሂደት ላይ ነው። ባለፉት አምስት ወራት ውስጥ፣ ኮሚሽኑ ከ50 የሚበልጡ የማህበረሰብ መረጃ ክፍለ ጊዜዎችን፣ የማህበረሰብ የዳሰሳ ጥናት፣ እና በሰባት ህዝባዊ የውይይት መድረኮችን በማስተናገድ ወይም በመሳተፍ ስለ ድጋሚ የወረዳ ማከፋፈሉ ሂደት እና በሰፈር ላይ ተጽእኖ ለማድረግ ስላለው አቅም ከህዝቡ ግብረ-መልሶችን መሰብሰብ ችሏል። ይህ ሂደት ኮሚሽኑ አዲስ የከተማ ምክር ቤት ወረዳዎች ድንበሮችን አንድ ረቂቅ ካርታ ሥራ ላይ እንዲያውል አስችሎታል። የህብረተሰቡ አባላት በረቂቅ ካርታው እና በታቀደው የወረዳዎች ወሰኖች ላይ የህዝብ አስተያየት እንዲያቀርቡ ተጋብዘዋል።

የሲያትል ድጋሚ የወረዳ ማከፋፈል ኮሚሽን ሰብሳቢ ግሬግ ኒኬልስ (Greg Nickels)፣ "በሲያትል ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰባት ከተማ ምክር ቤት ወረዳዎችን መስመሮች እንደገና በመቅረጽ ላይ ተሰማርተናል" ብለዋል። "ሥራችንን በምንሠራበት ወቅት እኔና የሥራ ባልደረቦቼ ኮሚሽነሮች ሕዝቡን ለማዳመጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ እያደረግን ነው። በዚያን ሂደት ውስጥ ረቂቅ ካርታ መቀበል/ ሥራ ላይ ማዋል ትልቅ እርምጃ ነው።"

የኮሚሽኑ ረቂቅ ካርታ ነሐሴ 2 በሲያትል መልሶ የወረዳ ማከፋፈያ ኮሚሽን ግልጽ ህዝባዊ ስብሰባ ላይ የተፈጠረ ሲሆን ባለፉት አምስት ወራት ውስጥ በቀረቡት የህዝብ አስተያየቶች የተነገረ ነው። ካርታው የከተማ ሕገ-መንግስት/ቻርተር እና በስቴት/ግዛት የታዘዙ መስፈርቶችን የሚከተል የመልክዐ-ምድራዊ መረጃ ስርዓት (GIS) የባለሙያ እውቀትን እና የ2020 የሕዝብ ቆጠራ መረጃን በመጠቀም አዲስ ድንበሮችን ለመሳል እና ውሱን፣ ተከታታይ እና በህዝብ ብዛት እኩል የሆኑ ወረዳዎችን ለማቋቋም ነው። ደግሞም ካርታው፣ በተጨባጭም መጠን፣ እንደ አሁን ያሉትን የወረዳዎች ድንበሮች መከተል፣ የውሃ መስመሮችን እና የመልክዐ-ምድራዊ ድንበሮችን ማወቅ፣ እና በተቻለ መጠን የሲያትል ነባር ማህበረሰቦችን እና ተጎራባቾችን እንዳሉ ለማቆየት የመሳሰሉትን ተጨማሪ ነገሮች ያካትታል።

### የህዝብ አስተያየት

የመጨረሻው የካርታ ረቂቅ ውይይት አሁን ይጀመራል እና ሁለቱም የህዝብ አስተያየት እና ተሳትፎ በሲያትል የወረዳ መልሶ ማከፋፈያ ኮሚሽን ይጠየቃሉ። የህዝብ አባላቱ የመጨረሻውን የካርታ ረቂቅ በመገምገም በ https://www.seattle.gov/redistricting/how-to-partipate ላይ አስተያየት መስጠት ይችላሉ።

በአሁኑ ጊዜ ህዳር 8 ቀን 2022 እንዲሆን የታቀደው እና ከህዳር 15 ቀን 2022 የማያልፈው፣ የተሰየመው የህዝብ አስተያየት መስጫ ጊዜው ከነሐሴ 3 ቀን 2022 ጀምሮ ኮሚሽኑ የመጨረሻውን የወረዳ እቅድ እስከሚያቀርብበት ቀን ድረስ ክፍት ነው።

የረቂቁን ካርታ አካላዊ ቅጂ ማግኘት ከፈለጉ፣ እባክዎን ሎገን ድራሞንድ (Logan Drummond)ን በ Logan.Drummond@seattle.gov ያግኙ። እንዲሁም አንድ ቅጂ ከፈለጉ በ600 አራተኛ ጎዳና ላይ በሚገኘው፣ በሲያትል ከተማ አዳራሽ የደንበኞች አገልግሎት ጠረጴዛ ማግኘት ይችላሉ።

የህዝብ አስተያየት በሚከተሉት መስጠት ይቻላል:

- ከሶስቱ የህዝብ የውይይት መድረኮች ውስጥ ባንዱ በአካል ተገኝተው
  - **ህዝባዊ የውይይት መድረክ #1: ማክሰኞ፣ ነሐሴ 9ኛ፣ ከ12:00 - 1:30 ከሰዓት**
    አካላዊ ቦታ: የሲያትል ከተማ አዳራሽ፣ 600 አራተኛ ጎዳና፣ ቦርዶች እና ኮሚሽኖች ክፍል L280
    ምናባዊ አገናኝ: https://us06web.zoom.us/j/84697105761
  - **የህዝብ የውይይት መድረክ #2: መስከረም – ቀን እና ሰዓቱ ወደፊት የሚታወቅ (TBD)**
  - **የህዝብ የውይይት መድረክ #3: ጥቅምት – ቀን እና ሰዓቱ ወደፊት የሚታወቅ (TBD)**

- በመደበኛነት የጊዜ ስሌዳ በተያዘለት የሲያትል የወረዳ መልሶ ማከፋፈያ ኮሚሽን ስብሰባ በአካል ተገኝቶ። ለቀናት እና ለሰዓታት የሲያትል የወረዳ መልሶ ማከፋፈያ ኮሚሽን ድህረ ገጽን ይመልከቱ።
- የሲያትል የወረዳ መልሶ ማከፋፈያ ኮሚሽን የህዝብ አስተያየት ማቅረቢያ ቅጽ በመጠቀም በጽሁፍ።

ለበለጠ መረጃ ወይም ለማንኛዉም የህዝብ የውይይት መድረኮች የትርጉም አገልግሎትን ለመጠየቅ፣ እባኮትን ኤልሳ ባትረስ-ቦኒ (Elsa Batres-Boni)ን በ Elsa.Batres-Boni@seattle.gov ወይም (206) 256-6198 ያግኙ።

ስለ የሲያትል የወረዳ መልሶ ማከፋፈያ ኮሚሽን ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት http://www.seattle.gov/redistricting ን ይጎብኙ።

# # #